የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፵
አዲስ አበባ ሐምሌ ፰ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. 40
ADDIS ABABA 15th July, 2026

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፲፮/፪ሺ፲፰
የኅብረት ሥራ ማህበራት (ማሻሻያ) አዋጅ …………………………………………………...ገጽ ፲፱ሺ፰፻፲፰

Content

Proclamation No. 1416/2026
Cooperative Societies (Amendment) Proclamation................................Page 19818

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፲፮/፪ሺ፲፰

የኅብረት ሥራ ማህበራት (ማሻሻያ) አዋጅ

የሀገራችን የኅብረት ስራ ማህበራት ዝቅተኛ ካፒታል እና የአባላት ቁጥር ያሏቸው እና ተበታትነው የተደራጁ በመሆኑ በመቀላቀል በኢኮኖሚው ተወዳዳሪ ኅብረት ስራ ማህበራትን መፍጠር በማስፈለጉ፤

የኅብረት ስራ ማህበራት በኢኮኖሚው ላይ ትርጉም ባለው መልኩ የግብይት ተሳትፏቸውን ከፍ ለማድረግ፣ ምርትና ምርታማነትን በመጨመር የወጪ ንግድ ድርሻቸውን ለማሳደግ፣ የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ፣ ከአባላት ውጪ ዕጣ የሚሸጡበትን ስርዓት ለመዘረጋት፣ የጋራ ኢንቨስትመንት ለማበረታታት፣ የካፒታል አቅም ለማሳደግ፤ ጠንካራ የቁጥጥር ሥርዓት ለመገንባት፣ የኦዲት ተደራሽነትን ለማረጋገጥ፣ የሴቶች፣ የወጣቶች እና የአካል ጉዳተኞች አካታችነትን እውን ለማድረግ እና የኅብረት ስራ ፈንድ ተግባራዊ ለማድረግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክረሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፮) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

PROCLAMATION NO. 1416/2026

COOPERATIVE SOCIETIES (AMENDMENT) PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary our country's cooperatives have low capital and a small number of members, and they are organized scattered due to the necessity to have a bargaining power on the economy through mergers;

WHEREAS, it has become necessary to increase the participation of cooperatives in the market in a way that brings meaningful change to the economy, it is necessary to reduce inflation, increase production and productivity, and expand their share in export trade. It is also important to strengthen their capital capacity, establish a system that allows the sale of shares to non-members, encourage joint investment, build a strong regulation system, and ensure access to auditing. Furthermore, it is required to realize the inclusion of women, youth, and persons with disabilities, and to make the cooperative fund operational;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (6) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia It is hereby declared as follows.

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የኅብረት ሥራ ማህበራት (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፲፮/፳፻፲፰” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. **ማሻሻያ**

፩/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ ፲ ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ ፲ ተተክቷል:-

፲/ **“አባል”** ማለት በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት እንደኅብረት ሥራ ማህበሩ አይነት የተደነገጉትን የአባልነት መመዘኛዎችን በማሟላት ለአባልነት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያገኘ ግለሰብ ወይም መሰረታዊ የኅብረት ስራ ማህበር ወይም የኅብረት ስራ ማህበራት ዩኒዬን ወይም የኅብረት ስራ ማህበራት ፌዴሬሽን ወይም ህጋዊ ሰውነት ያለው ተቋም ነው።

፪/ የአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳) ተሰርዞ በአዲስ ንዑስ አንቀፅ (፳) ተተክቷል:-

፳/ “**አግባብ ያለው ባልስልጣን**” ማለት የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ወይም በክልል የኅብረት ሥራ ማህበራትን አዋጅ ለማስፈጸም፣ ዘርፉን ለመምራትና ለመቆጣጠር የተቋቋመ አካል ነው።

፫/ **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ማንኛውም ክልል እና በንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት አዲስ የተቋቋሙትንና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤

፬/ ከአዋጁ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፳፫) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፳፬)፣ (፳፭) እና (፳፮) ተጨምረዋል፣ ነባሮቹ ንዑስ አንቀፆች (፳፬) እና (፳፭) እንደቅድም ተከተላቸው (፳፯) እና (፳፰) በመሆን ተሸጋሽጓል፤

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as “Cooperative Societies (Amendment) Proclamation No.1416/2026”.

2. **Amendment**

1/ Sub-Article (10) of Article 2 of the Proclamation, is hereby amended as follows:

10/ **"Member"** means an individual or a primary Cooperative Society or Union or Federation or Institution with legal entity that has applied for membership and has been admitted by the Cooperative in accordance with the Cooperative's By Laws and has met the membership criteria prescribed by the Cooperative type.

2/ Sub-Article (20) of Article 2 of the Proclamation has been delated and replaced by new Sub-Article (20):

20/ "**Appropriate Authority**" means the Ethiopian Cooperative Commission or an organ established at Regional levels to execute the Cooperative Society’s Proclamation lead and regulate the Cooperatives.

3/ **"Region"** means any state referred to in Sub-Article (1) of Article 47 and newly formed in accordance to Sub-Article (2) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and includes Addis Ababa City Administration and Dire Dawa Administration;

4/ New Sub-Articles (24), (25) and (26) have been added after Sub-Article (23) of Article 2 of the Proclamation, and Sub- Articles (24), (25) have been renumbered as (27) and (28) respectively;

፳፬/ **"መቀላቀል"** ማለት አንድን የኅብረት ሥራ ማህበር አስፈላጊውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ከሌላ ተመሳሳይ ዓላማና ተግባር ካለው የኅብረት ሥራ ማህበር ጋር አንድ እንዲሆን በማድረግ የአንዱን የኅብረት ስራ ማህበር ህልውና ማሳጣት ነው።

፳፭/ **"በልዩ ሁኔታ የሚደረግ ኦዲት"** ማለት የኅብረት ሥራ ማህበር የኦዲት ወጪ መሸፈን እንደማይችል ሲታመን ወይም እንዲፈርስ ሲወሰን ወይም የተደረገውን ኦዲት ለማረጋገጥ ሲያስፈልግ ወይም በፍርድ-ቤት ሲታዘዝ ወይም ስጋትና ጥቆማ ሲኖር አግባብ ያለው ባለስልጣን የኦዲት ወጪውን ሸፍኖ በልዩ ሁኔታ ኦዲተር መድቦ ኦዲት ማድረግ ነው።

፳፮/ **"ተቋም"** ማለት የአባልነት መስፈርት አሟልቶ የመሠረታዊ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበር አባል ሊሆን የሚችል ሕጋዊ ሰውነት ያለው መንግስታዊ ያልሆነ አገልግሎት ሰጪ ወይም አምራች ነው።

፭. አንቀፅ ፯ ንዑስ አንቀፅ (፭) ተሰርዞ በሚከተለው ንዑስ አንቀፅ (፭) ተተክቷል። አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፮) እና (፯) ተጨምሯል፦

፭/ ማንኛውም መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበር እንደ ኅብረት ስራ ማህበራቱ ዓይነት ወይም የስራ ባህሪ እና የኢኮኖሚያዊ አዋጭነት በቀበሌ ፣ በተቋም ፣ በወረዳ፣ በዞን ፤ በክልል ወይም በፌዴራል ደረጃ ይደረጃሉ።

፮/ በተመሳሳይ ተግባር ላይ የተደራጁ መሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት ወይም ዩኒዬኖች ወይም ፌዴሬሽኖች ሊቀላቀሉ ይችላሉ።

24/ **"Merging"** means whereby a Cooperative Society, upon meeting the necessary requirements, join with another Cooperative Society having similar objectives and functions, thereby terminating the legal existence of one of the Societies.

25/ **"Special Audit"** means that when it is believed that the Cooperative can not cover the Audit costs, or when it is decided to dissolve, or when it is necessary to verify the audit conducted, or when it is ordered by a Court, or when there are risks and propositions, an Appropriate Authority conduct Audit by covering the Audit costs under special circumstances.

26/ **"Institution"** means a Non-Governmental service providing or producing organization that has legal personality and fulfills the membership requirements to become a member of a primary Savings and Credit Cooperative Society.

5. Article 7 Sub-Article (5) is deleted and replaced by the following Sub-Article (5). new Sub-Articles (6) and (7) have been added፡

5/ Any primary Cooperative Society shall be organized at the Kebele, Institution, Woreda, Zone, Regional, or Federal level, depending on the type of Cooperative Society, and the nature of its work or economic viability.

6/ Primary Cooperative Societies, Unions, or Federations that are organized for the same purpose may have a right to merge together.

፯/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፭) እና (፮) ዝርዝር አፈፃፀም መመሪያ ሊወጣ ይችላል።

፰/ መሰረታዊ የኅብረት ሥራ ማህበራት አደረጃጀት በአዋጁ አንቀጽ ፯ ንዑስ አንቀጽ ፪(ሀ) ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሴቶች ወይም አካል ጉዳተኞች ወይም ወጣቶች ያለባቸውን የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ችግሮቻቸውን ለመፍታት ከሚሰሩት ልዩ ሥራ ባህሪ በመነሳት በሴት አባላት ወይም በአካል ጉዳተኞች ወይም ወጣቶች ብቻ ኅብረት ሥራ ማህበር ሊመሰረቱ ይችላሉ።

፱/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፰) የተጠቀሰው ቢኖርም አባልነት ለሁሉም ሰው ክፍት መሆኑን በኅብረት ሥራ ማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መወሰን አለበት።

፮. የአዋጁ አንቀጽ ፱ ርዕስ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፦

፱. የኅብረት ሥራ ማህበር ሥም እና የሥራ ክልል፡፡

፯. የአዋጁ አንቀጽ ፱ ከንዑስ አንቀጽ (፭) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፮) እና (፯) እና (፰) ተጨምሯል፤

፮/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር በመተዳደሪያ ደንቡ ላይ የተወሰነ የራሱ የሥራ ክልል ይኖረዋል።

፯/ ኅብረት ስራ ማህበራት የሥራ ክልላቸውን ለማሻሻል ሲፈልጉ አግባብ ያለው ባለስልጣን በማስፈቀድ ማሻሻል ይችላሉ።

፰/ ኅብረት ስራ ማህበራት በስራ ክልላቸውም ሆነ ከስራ ክልላቸው ውጪ ቅርጫፍ ለመክፈት ሲፈልጉ አግባብ ያለው ባለስልጣን በማስፈቀድ ቅርንጫፍ ለመክፈት ይችላሉ፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

7/ Directives for the detailed implementation of Sub-Articles (5) and (6) of this Article may be issued.

8/ without prejudice to the Provision stated in Article 7, of Sub-Article 2(a) of this Proclamation, women, persons with disabilities, or youth may establish a primary Cooperative Society composed only of women members, or only persons with disabilities, or only youth, based on the special nature of the activities they undertake to solve their economic, social, and cultural problems.

9/ Notwithstanding the provision stated in Sub-Article (8) of this Article, the By-Laws of the Cooperative Society must stipulate their decision that membership is open to all persons.

6. Article 9 of the Proclamation title is amended as follows:

9. Name of the Cooperatives and working area.

7. New Sub-Articles (6), (7) and (8) have been added after Sub-Article (5) of Article 9 of the Proclamation;

6/ Any Cooperative Society shall have its own defined area of operation as specified in it’s By Laws.

7/ Any Cooperative Society that wishes to amend its area of operation may do so by obtaining approval from the Appropriate Authority.

8/ When Cooperative Societies wish to open branches within or outside their area of operation, they may do so by obtaining approval from the Appropriate Authority. detailed implementation shall be determined by Directives issued by the Ministry.

፰. በአዋጁ አንቀጽ ፲፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፦

፪/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ዩኒዬን እንደ ኅብረት ስራ ማህበራቱ ዓይነት ወይም የስራ ባህሪ ወይም የኢኮኖሚያዊ አዋጭነት እየታየ በዞን ወይም በክልል ወይም በፌዴራል ደረጃ ይደራጃሉ።

፱. የአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደል ተራ (ሀ) ተሰርዞ እንደገና ተስተካክሎ ቀርቧል፦

ሀ) ለአባል ኅብረት ሥራ ማህበራት ዩኒዬኖች የኦዲት አገልግሎት ማመቻቸት፣

፲. የአዋጁ አንቀጽ ፳፩ ከንዑስ አንቀጽ (፲) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲፩) ተጨምሯል፦

፲፩/ የኅብረት ሥራ ማህበራት የሥራ አመራር ኮሚቴ የሚያማክሩ አማካሪ ባለሙያዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙን በተመለከተ መመሪያ ይወጣል፡፡

፲፩. የአዋጁ አንቀፅ ፳፫ ርዕስ እንደገና ተስተካክሎ ቀርቧል፤

ከአባላት ውጭ ስለሚሰጥ አገልግሎት እና የጋራ ኢንቨስትመንት ስለመግባት

፲፪. ከአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፤ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ እና ንዑስ አንቀጽ ፫ ተጨምሯል፣ ንዑስ አንቀጽ (፪) ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ ተሸጋሽጓል፤

፪/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከግሉ ዘርፍ ጋር የሚያደርጉት የጋራ ኢንቨትመንት በጠቅላላ ጉባዔ ልዩ ውሳኔ እና የተቋቋሙበትን ዓላማና ተግባር መሠረት በማድረግ በሚከተሉት የኢንቨስትመንት መስኮች ላይ ይሆናል፦

8. Sub-Article (2) of Article 14 of the Proclamation has been delated and replaced by new Sub-Article (2)፡

2/ Any Cooperative Society may be organized as a Union at the Zonal, Regional, or Federal level, depending on the type, the nature of work of the Cooperative or economic visibility.

9. Sub-Article 4 letter (a) of Article 21 of the Proclamation delated and replaced as follows፡

a) Arrange Audit services to members of Cooperative Societies Unions,

10. A new Sub-Article 11 is added, after Sub-Article (10) of Article 21 of the Proclamation፡

11/ The Management Committee of Cooperatives Societies may use advisory experts to advise them, implementation Directive shall be issued.

11. The title of Article 23 of the Proclamation has been modifed as follows;

About services provided to non-members and entering into joint investments.

12. New Sub-Articles (2)(a), (b), (c), (d), (e) and (3) have been added after Sub-Article (1) of Article 23 of the Proclamation, and Sub-Article (2) has been renumbered as Sub-Article (4);

2/ Cooperative Societies conducting joint investment with the private sector, shall be request special resolution and the organizational objectives and functions of Cooperative Societies, joint investment focus on the following investment areas:

ሀ) በግብርና ምርት ማምረት ወይም ግብይት ወይም ማቀነባበር ወይም ፋብሪካዎች ወይም ሜካናይዘሽን ዘርፍ፣

ለ) በትራንስፖርት ወይም መሰረተ-ልማት ወይም ፋይናንስ ዘርፍ፣

ሐ) በኢነርጂ አቅርቦት ወይም ኮንስትራክሽን ወይም በማዕድን ዘርፍ፣

መ) በማህበረሰብ አቀፍ ተፋሰስ ወይም የአየር ንብረት ለውጥ ወይም በቱሪዝ ም አገልግሎት፣

ሠ) አግባብ ያለው ባለስልጣን በጥናት በሚለያቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች ሊሳተፍ ይችላል።

፫/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ከግሉ ዘርፍ ጋር ስለሚያደርጉት የጋራ ኢንቨስትመ ንት የኅብረት ስራ ማህበራት ድርሻ ስልሳ ከመቶ እና የኢንቨሰተሮች ድርሻ አርባ ከመቶ መብለጥ የለበትም። በሰነድ አረጋጋጭ አካል በተመዘገበ ውል ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት።

፲፫. ከአዋጁ አንቀጽ ፳፬ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተጨምሯል፣ ንዑስ አንቀጽ (፫) ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኖ ተሸጋሽጓል፣

፫/ ተቋማት የመሰረታዊ ቁጠባና ብድር ኅብረት ሥራ ማህበራት አባላት ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለአፈጻጸሙ ዝርዝር መመሪያ ይወጣል፡፡

፲፬. የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ከንዑስ አንቀጽ (፱) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፲) እና (፲፩) ፊደል ተራ (ሀ)፣ (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ)፣ (ሠ) ተጨምሯል፣

a) Agricultural production or marketing, Agro-processing or manufacturing industry or mechanization sector;

b) Transportation, or infrastructure, or Finance, sector;

c) Energy supply, or Construction, Mining sector;

d) Community watershed develop ment or climate change resilience or tourism service;

e) It may participate in investment sectors identified by the Appropriate Authority through studies.

3/ In joint investments between Cooperati ves and the private sector, the share of the Cooperatives must not exceed 60 (Sixty) percent, and the share of the investors must not exceed (Forty) 40 percent; the agreement must also be based on a contract registered by a notary body.

13. A new Sub-Article (3) is added after Sub-Article (2) of Article 24 of the Proclamation, and Sub-Article (3) is renumbered as Sub Article (4);

3/ Institutions may become members of primary Savings and Credit Cooperatives. The Appropriate Authority shall issue a Directive for its implementation.

14. New Sub-Articles (10) and (11) (a), (b), (c), (d), (e), (f) have been added after Sub- Article (9) of Article 27 of the Proclamation.

፲/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ካፒታል ለማሳደግ አባል ላልሆነ ሰው ዕጣ መሸጥ ይችላል፡፡ ሆኖም የሚሸጠው ዕጣ ከታወጀው ጠቅላላ ዕጣ ከአስር ከመቶ መብለጥ የለበትም።

፲፩/ የኅብረት ሥራ ማህበር ዕጣ የገዛ አባል ያልሆነ ሰው የሚከተሉት መብትና ግደታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) በገዛው የዕጣ መጠን መሠረት የትርፍ ክፍፍል ያገኛል፤

ለ) የኅብረት ሥራ ማህበሩ ከከሰረ የኪሳራው ተጋሪ ሊሆን አይችልም፤

ሐ) የገዛው እጣ እንዲሰጠው በጠየቀ በ፮ ወር ውስጥ የማግኘት፤

መ) የመምረጥና የመመረጥ መብት አይኖረውም፤

ሠ) የኅብረት ስራ ማህበሩን ህልውና የሚያሳጣ ስራ ያለመስራት።

፲፭. የአዋጁ አንቀጽ ፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፩) ተተክቷል፤

፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ቢያንስ በዓመት አንድ (፩) ጊዜ የጠቅላላ ጉባዔ ማድረግ አለበት።

፲፮. የአዋጁ አንቀፅ ፴፬ ንዑስ አንቀፅ (፯) በአዲስ መልክ እንደገና ተሻሽሎ ቀርቧል፤ በተጨማሪም ከድንጋጌው ቀጥሎ ሁለት አዲስ ንዑስ አንቀጾች (፰) እና (፱) ሆነው ተጨምረዋል፡-

፯/ ቁጥራቸው የሚፈቅድ አባል ሴቶች በሚገኙበት ማንኛውም የኅብረት ስራ ማህበር ውስጥ ቢያንስ ፶ (ሃምሳ) ከመቶ አመራር በሴት አባላት መያዝ አለበት።

10/ Any Cooperative Societies may sell shares to a non-member to increase its capital. however, the number of shares sold shall not exceed 10 (Ten) percent of the total number of shares declared.

11/ A non-member who has purchased a share of the Cooperative Societies shall have the following rights and obligations:

a) shall receive a dividend based on the amount of the share purchased;

b) The Cooperative goes bankrupt, shall not be sharer of bankrupt;

c) A right to obtainin within 6 months upon requesting to obtain the purchased share,

d) Shall not have the right to vote or be elected;

e) Prohibition of an act against the existence of Cooperative Society.

15. Sub-Article (1) of Article 33 of the Proclamation has been deleted and replaced by the new Sub-Article (1) as follows;

1/ Any Cooperative shall hold a General Assembly meeting at least once in a year.

16. Sub-Article (7) of Article 34 of the Proclamation has been amended as follows; besides to that new Sub-Articles (8) and (9) have been added፡

7/ In any Cooperative Society where there are sufficient number of female members, at least 50 (Fifty) percent of the Leadership positions must be held by women members.

፰/ ቁጥራቸው የሚፈቅድ አባል ወጣቶች በሚገኙበት ማንኛውም የኅብረት ስራ ማህበር ውስጥ ቢያንስ ፲ (አስር) ከመቶ አመራር በወጣቶች አባላት መያዝ አለበት።

፱/ ቁጥራቸው የሚፈቅድ አባል አካል ጉዳተኞች በሚገኙበት ማንኛውም የኅብረት ስራ ማህበር ውስጥ ቢያንስ ፲ (አስር) ከመቶ አመራር በአካል ጉዳተኛ አባላት መያዝ አለበት፡፡

፲፯. የአዋጁ አንቀፅ ፴፱ ንዑስ አንቀፅ (፫) እንደገና ተስተካክሎ ቀርቧል፦

፫/ ሥራ አስኪያጁ የኅብረት ሥራ ማህበሩን የዕለት ተዕለት ተግባራት መምራት፣ በተሰጠው የሥራ ዝርዝር እና ውክልና መሠረት በሥራ አመራር ኮሚቴ የሚሰጡትን ሥራዎች በግልጸኝነት፣ በተጠያቂነት እና በሙሉ ኃላፊነት ማከናወን አለበት፡፡

፲፰. የአዋጁ አንቀጽ ፵፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀፅ (፪) ተተክቷል፤

፪/ ለመጠባበቂያ ከተቀነሰ በኋላ የተጣራ የትርፍ ክፍፍል ፫ ከመቶ ለኅብረት ሥራ ፈንድ የሚውል ሲሆን ቀሪው ስልሳ ሰባት ከመቶ የኅብረት ሥራ ማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በሚወስነው መሰረት የሚከፋፈል ይሆናል።

፲፱. የአዋጁ አንቀጽ ፶ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አቀፆች (፩)፣(፪) ፣ (፫)እና (፬) ተጨምረዋል፣ ነባሮቹ ንዑስ አንቀፆች (፪)፣(፫)፣(፬) እና (፭) በቅድም ተከተላቸው (፭)፣ (፮)፣ (፯) እና (፰) ሆነው ተሸጋሽገዋል፦

፩/ ማንኛውም የኅብረት ሥራ ማህበር ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የኦዲት ወጪውን ሸፍኖ ሂሳቡን ኦዲት ማስደረግ አለበት።

8/ In any Cooperative Society where there are sufficient number of youth members, at least 10 (Ten) percent of the Leadership positions must be held by youth members.

9/ In any Cooperative Society where there are sufficient number of members with disabilities, at least 10 (Ten) percent of the Leadership positions must be held by members with disabilities.

17. Sub-Article (3) of Article (39) of the Proclamation has been modifed as follows፡

3/ The Manager shall lead the day-to-day operations of the Cooperative Society; he must perform tasks assigned under his job description and delegation, as well as duties given by the Management Committee, with transparency, accountability and full responsibility.

18. Sub-Article (2) of Article 45 of the Proclamation has been delated and replaced by new Sub-Article (2) as follows;

2/ After deduction for reserves, the net profit shall be allocated 3 (Three) percent to the Cooperative Fund, and the remaining 67 (Sixty Seven) percent shall be distributed based on the decision made by the General Assembly of the Cooperative.

19. Sub-Article (1) of Article 50 of the Proclamation has been delated and new Sub-Articles (1), (2),(3) and (4) have been added, while Sub-Articles (2), (3), (4) and (5) have been renumbered as (5), (6) , (7) and (8) respectively፡

1/ Any Cooperative Societies must Audit its financial statements at least once in a year, by covering the cost of the audit.

፪/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ኦዲት የሚደረገዉ በኅብረት ሥራ ሊግ ፣ በኦዲት ሙያዎች በተደራጀ የኅብረት ሥራ ማህበር ወይም ህጋዊ የኦዲት ፈቃድ ባለው ሰው ነው።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተደነገገዉ ቢኖርም አግባብ ያለው ባለስልጣን በልዩ ሁኔታ የኅብረት ሥራ ማህበራት ሂሳብ ኦዲት ማድረግ ይችላል።

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ያለው ባለስልጣን ህጋዊ ፈቃድ ያላቸው ኦዲተሮችን ይለያል፣ የኦዲት ሂደትን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ በትክክል መሰራቱን ያረጋግጣል፣ ስህተት ሲኖር ማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፣ ለጉባኤ አስቀርቦ እንዲጸድቅ ያደረጋል፣ ስለ አፈጻጸሙ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

፳. ከአዋጁ አንቀጽ ፶፪ ንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀፆች (፭) ፣ (፮) እና (፯) ሆነው ተጨምሯል:-

፭/ የቁጠባና ብድር የኅብረት ሥራ ማህበራት የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች አግባብ ባለው ባለስልጣን በሚወጣ መለኪያ ስታንዳርድ መሠረት ኢንስፔክት ይደረጋል፡፡

፮/ የኅብረት ሥራ ማህበራት ኢንስፔክት ሲደረግ አዋጁን፣ ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም የሚወጡ ደንብና መመሪያዎችን ተላልፈው በሚገኙ ኅብረት ስራ ማህበራት፣ የኅብረት ስራ ማህበራት አመራር ኮሚቴ፣ ስራ-አስኪያጆች እና ቅጥር ሰራተኞች ላይ አግባብ ያለው ባለስልጣን አስተዳደራዊ ማስተካከያ እርምጃ ይወሰዳል። ዝርዝር አፈጻጸሙም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ ይወሰናል፡፡

2/ The accounts of Cooperative Societies shall be audited by a Cooperative League or a Cooperative Society organized in the Auditing profession, or a person who has a Legal auditing license.

3/ Notwithstanding the provision stated in Sub-Article (2) of this Article, the Appropriate Authority may, in special circumstances, audit the financial statements of Cooperatives Societies.

4/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the Appropriate Authority shall identify Legally licensed Auditors; monitor, supervise, and ensure the proper conduct of the auditing process; take corrective measures when errors occur; present the Audit for approval to the General Assembly; and issue detailed Directives regarding its implementation.

20. The following Sub-Articles (5), (6) and (7) are added after Article 52, of Sub-Article (4) of the Proclamation:

5/ The activities of savings and credit Cooperative Societies shall be inspect prudentially with measurement standards issued by the Appropriate Authority.

6/ When the Appropriate Authority conducts an inspection of Cooperative Societies, it shall take administrative corrective measure against Cooperative Societies, their Management Committes, Managers, employed staffs who are found to have violated the Proclamation and the Regulations and Directives issued for the implementation of this Proclamation. The detailed procedures for the implementation of such administrative corrective measures shall be determined by a Regulation to be issued by the Council of Ministers.

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) ያለው እንደተጠበቀ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ሌሎች አካላት ህጋዊ እርምጃ እንዲወስዱ ይደረጋል፡፡

፳፩. የአዋጁ አንቀፅ ፸ ንዑስ አንቀፅ (፩) እንደገና ተሻሽሎ ቀርቧል፣ በተጨማሪም አዲስ ሁለት ንዑስ አንቀጾች (፪)እና (፫) ሆነው የገቡ ሲሆን ሌሎቹ ንዑስ አንቀጾችም በቅደም ተከተል ተሸጋሽገዋል:-

፩/ የኅብረት ስራ ማህበራትን በሀገር አቀፍ ደረጃ ያደራጃል፣ያጠናክራል፣ ዲጅታላይዝ በሆነ ሥርዓት ይመዘግባል፣ ያድሳል፣ ይቆጣጠራል፣ ይሰርዛል፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ኅብረት ስራ ኮሚሽን ሀገር አቀፍ ተፈፃሚነት ያለው የኅብረት ስራ ማህበራት ሀገረዊ መረጃዎችን ለመያዝ ዲጅታላይዝ መረጃ ማዕከል ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣ መረጃዎችን ይተነትናል ለህዝብ ክፍት እንዲሆንም ያደርጋል፡፡

፫/ አግባብ ያለው የክልል ባለስልጣን የኅብረት ስራ ማህበራትን የምዝገባ ምስክር ወረቀት ምዝገባ ፣ እድሳት፣ ስረዛ ያከናውናል መረጃዎችን በዲጅታላይዝ የመረጃ ማዕከል የመረጃ ቋት ያስገባል፡፡ ስለዝርዝር አፈፃጸሙ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

፫. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ሐምሌ ፯ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት

7/ Without prejudice to the provision stated under Sub-Article (6) of this Article, when deemed necessary, other relevant bodies shall cause to take legal action.

21. Sub- Article (1) of Article 70 of the Proclamation has been amended with a new sub-Article (1). Additionally new Sub-Articles (2) and (3) have been added; and the subsequent Sub-Articles have been renumbered respectively:

1/ It organizes Cooperative Societies at a national level, strengthens and registers, renews, cancels, and regulates through a digitalized system.

2/ The Ethiopian Cooperative Commission establishes a digital data center to collect national data from cooperatives with nationwide operations, manages it, make analaysis of the information and made accessible to the public.

3/ The Appropriate Regional Official make registration of Cooperatives' registration certificates, renewals, cancels, and enter basic Cooperative Society data into the digital data center. The detailed implematation detrmined with Directive issued by the Ministry.

3. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, On this 14th day of July, 2026

TAYE ATSKESELASSIE

PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA